# የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት
# Ethiopian Democratic Union

429 N St., SW # S-304 Washington, D.C. 20024 * Phone / Fax: 202-479-9062
e-mail: edunasupport@gmail.com * web: www.ethiopiandemocraticunion.org

**ከኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ኅብረት (ኢድኅ/ኢዲዩ)**
**የተሰጠ መግለጫ**

**ሰኔ 17 ቀን 1999 ዓ.ም**

**አይቀሬው ሕዝባዊው ድል ለአድርባዮች ቅዠት ነው።**

**ሰኔ 8 ቀን 1999 ዓ.ም የመንግስት መገናኛ ብዙሀን የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን፣ ሬዲዮ ጣቢያዎችና የተለያዩ ልሣናት ሣይቀር በቅብብሎሽ አራት የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ህብረት አባላትን ድርጅቱ ማባረሩንና ለዚህም የሠጠው ምክንያት አራቱ ግለሰቦች በጎረቤት ሀገራት (ሱዳንና ኬንያ) በመንቀሳቀስ ሀገሪቱን ወደ ጦርነት የሚከትና ብጥብጥ የሚፈጥር የጦርነት ቅስቀሳ ሲያደርጉ በተጨባጭ ስለተደረሰባቸው ነው የሚለው መግለጫ በግራዝማች ካህሳይ ፊርማ በድርጅታችን ስም የተሰጠ መሆኑን አረጋግጠናል።**

**የሕዝባችን ብሶትና እንግልት፣ አፈናና እመቃ፣ እስራትና ግድያ ብሎም የሀገራችን አስጨናቂውና አደገኛ ጉዞ ከማይታያቸው ሆድ አደር ጥቅመኞች የሚጠበቅና የተለመደ ቢሆንም ሽማግሌ በጠፋበት ዘመን የ70 ዓመቱ አዛውንት ለዚህ እኩይ ተግባር ማስፈፀሚያ መሳሪያ ሆነው ሲታይ እንደ ዜጋ ሁላችንንም ያሽማቅቃል፣ አሳፋሪና ነውርም ነው።**

**የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ እንዲሉ ለመሆኑ በዚህ መሠሉ እንቅስቃሴ ዙሪያ መግለጫ የመስጠቱም ሆነ እርምጃ የመውሰዱ ተግባርና ግዴታ የአገዛዙ ነው ወይስ የግራዝማች ካህሳይን ምናልባትም አንድም ሁለትም እንዲሉ ተፈጥሮአዊ ማንነታቸውን በተግባር ለማሳየት ይሆን? ለማንኛውም በርካታ ተግባራት ቢኖሩም ንቀን በተውነው ተራ ጉዳይ ላይ አንድም ሰው ቢሆን በሚኖረው የመረጃ እጥረት ሣቢያ ግራ እንዳይጋባ በማሰብ ይህንን ማብራሪያ እንድናወጣ ተገደናል።**

**ስለሆነም:-**

**1ኛ) ግራዝማች ካህሳይ ዶሪ ከሌሎች 6 (ስድስት) ግብረ-አበሮቻቸው ጋር በመሆን ቀደም ሲል በሱዳን የነበረውን የኢዲዩ ንብረትና ታሪካዊ ሠነድ በካርቱም ለህውሀት ኤምባሲ የሀገር መግቢያ መደራደሪያ በማድረግና በማስረከብ መላ ታጋዩን በትነውና መጠለያ አሳጥተው በሠላም ወደ ሀገር ከገቡ በኋላ በ1995 ዓ.ም. ሰኔ ወር ኢዲዩ የሚባል ድርጅት የለም። ከዛሬ ጀበሮ በአቶ ልደቱ ከሚመራው ኢዴፓ ጋር ተዋህደናል። ስማችንም ኢዲአፓ ነው ሲሉ በታሪክና በህዝብ ፊት ሸራተን ሆቴል አወጁ፣ በውስኪ ተራጩ በየበረሀው የሚንከታተተው ታጋይና አባል ንብረቱን ያጣው ወገናችን በማያውቀውና ባልመከረበት ሁኔታ አሳልፈው ሰጡት። እናስ የዚህ**

አሳፋሪ ታሪክ ባለቤት የሆነ ግለሰብ በኢዲዩ ስም ለመናገር የሚያስችል የህግ ድጋፍና የሞራል ብቃት ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባልን? ፍርዱን ለሕዝባችን ትተነዋል።

**2ኛ** ታህሳስ ወር 1996 ዓ.ም. በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ የሚኖሩ የኢዲዩ አባላት ባደረጉት ብርቱ ጥረት የተጫነባቸውን ሁሉ ተቋቁመው ዳግም ኢድህ/ኢዲዩ እንዲያንሠራራና ህጋዊ ፈቃዱም እንዲመለስ አደረጉ። ሆኖም በዓመቱ መስከረም 24 ቀን 1998 ዓ.ም. የሕዝብ ድምጽ ይከበር፣ውሳኔና ፍላጎቱ ይረጋገጥ በሚለው ሕዝባዊ አቋማችን ሳቢያ በህውሀት ታጣቂዎችና በስርዓቱ ካድሬዎች ቅንብር ባፈሙዝ ቢሮአችን ተነጠቀ፣ንብረታችን ተዘረፈ፣አባሎቻችንና አመራሮቻችን ተሰደዱ ተገደሉ። ስለሆነም ከመስከረም 24 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ህጋዊ ቢሮአችን በአዲስ አበባ እና 54 ቅርንጫፍና ንዑሳን ቢሮዎቻችን በመላ አገሪቱ የተዘጉ መሆኑን በድጋሜ እየገለጽን የምናደርገው ሠላማዊ ትግል በሀገራችን የተረጋጋ የሕበረተሰባችን ኑሮ እስኪረጋገጥና መላ ሕዝባችንን ያሳተፈና አመኔታን ያረጋገጠ ህገ-መንግስታዊ ስርዓት እስኪሰፍን በጽናት እንቀጥላለን።

**3ኛ** ግራዝማች ካህሳይና ቢጤዎቻቸው የተቀጭበረበረ የህዝብ ድምጽ የለም፣ ለተቀዋሚው የተቸረው ወንበር ከበቂ በላይ ነው፣ የሕብረት ትግል አያስፈልግምና ከሕብረት ወጥተናል፣ እነ እከሌን ከድርጅቱ አባረናል፣የሱማሌው ጦርነት ህጋዊና ፍትሃዊ ነው ወዘተ በማለት አስታውቀዋል። እነ ግራዝማች የኢዲዩ አባላት እንዳልሆኑ ሁሉ ይህ አቋምም የድርጅታችን የኢዲዩ አቋምና እምነት አይደለም።

**4ኛ** ህዳር ወር 1997 ዓ.ም. በባህር ዳር ከተማ በታሪካችን ከ20 ዓመት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ባካሔድነው ታሪካዊው ጠቅላላ ጉባኤያችን የተመረጡ መሪዎች ፣ የታጋዩን ሙሉ ድጋፍና አመኔታን ያገኘው አመራራችን ሁኔታዎች ፈቅደዉ መላ አባላችን ሊያሠባሠብና ጉባኤ ሊጠራ የሚችልበት ተጨባጭ ሁኔታ እስኪፈጠር የነበረውን ኃላፊነት አጠናክሮ ይቀጥላል።

**5ኛ** ስለ ትጥቅ ትግል ምንነትና እንዴት ጠንቅቆ ለሚያውቀዉና ከሀገሪቱ የጦርነት አዙሪት ሰፊ ተመክሮውም ሆነ እውቀቱ ላለው ድርጅታችን ይህን መሰሉ አሉባልታ የማናፈሱ አላማ ይህን በማለት ከምትጣል ፍርፋሪ ጥምን ለማርካት ከርስን ለመሙላት ካልሆነ በቀር በትግል ስልት ዙሪያ ላይ የተደረገም ሆነ የተገለጸ ለውጥ የሌለና በሬ ወለደ አሉባልታ መሆኑን በግልጽ እያስቀመጥን መላ አባሎቻችን በጽናትና በቁርጠኝነት የሚያደርጉት ሰላማዊ ትግል ተጠናክሮ በመቀጠል ላይ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን።

**6ኛ** ዛሬ ትግሉ ከመቼውም ጊዜ በላይ መቀራረብን፣ መተማመንና በእጅጉ ክንድ ለክንድ መጣመርን ይጠይቃል። ኅብረታችን ወሳኝ ሕዝባዊ ጥያቄ ከፊቱ ተደቅኗል። እናም ኅብረታች ለላቀ ትግል ያለው ቁርጠኝነት እንደተጠበቀ ሆኖ ሀገራችንን ለማዳን ሕዝባችንን ለመታደግ ስንል በአንድነት ለአንድ ሕዝብ በጽናትና በአንድነት እንሰለፍ በማለት ጥሪያችንን በዚህ አጋጣሚ እያቀረብን ለምንለያባቸውና አሉን ለምንላቸው ድርጅታዊ አቋሞችና እምነቶች ፈራጅና ወሳኝ የሆነውን ሕዝባችንን በቅድሚያ ነጻ እናውጣ እንላለን።

በመጨረሻም በሀገር ውስጥ የምንገኝም ሆንን በውጭ የምትገኙ የኢዲኅ አባላት ከመቼውም ጊዜ በላይ በመሰባሰብና ከትላንትና እስከ ዛሬ ትግሉን ርስት ጉልት አድርገው በመጦሪያነት ሲጠቀሙበትና ሲፈልጉ ሲክዱት ከኖሩ አስመሳዮች በመጠበቅ በየበረሃው የወደቁ ክቡር ታጋዮቻችንን አርማ በማንገብ ለሀገራችን አንድነት፣ ነጻነትና ዲሞክራሲያዊ ፣ሕገ መንግስታዊ ስርዓት መመስረት የገባነውን ቃል ደግሞ በማደስ ከዲሞክራቲክ ኃይሎች ጎን ተሰልፈን የዜግነት ድርሻችንን እንድንወጣ በጥብቅ እናሳስባለን።

የኢድኅ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ<br>ሰኔ 17 ቀን 1999 ዓ.ም.

የከፋፋዮች ሴራ ይከሽፋል!!
ኢትዮጵያዊነት ሕያው የትግላችን መሰረት ነው!!